«ባሕር አየች፣ ሸሸችም፣ ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ። ተራሮች እንደ ኮርማዎች፣ ኮረብቶችም እንደ በጎች ጠቦቶች ዘለሉ»።

*(መዝ ፻፲፫ ፥ ፫)*

# ስምዐ ጽድቅ



## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች

፫ ርእሰ አንቀጽ

፭ ሪፖርታዥ

፯ ቤተ አብርሃም

፲፪ ቃለ መጠይቅ

፲፮ የሕፃናት ዓምድ

፲፰ ትዝብት

፳ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ


## ስምዐ ጽድቅ


የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ

ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# “የጥምቀት በዓል ለሀገራችን አንድነት ታላቅ ምሳሌ ነው”

*በካሣሁን ለምለሙ*

*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ*



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

‹‹ የጥምቀት በዓል ለሀገራችን አንድነት ታላቅ ምሳሌ ነው›› ሲሉ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ጥር ፲ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በጃንሜዳ በተከበረው የከተራ በዓል ላይ ተናገሩ፡፡

ቅዱስነታቸው አያይዘውም ‹‹ይህ በዓል በዩኒስኮ የማይዳሰሱ ቅርሶች የተመዘገበ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቅ እና ብዙ የውጭ ሀገር ጎብኚዎች የሚሳተፉበት በዓል ነው›› ብለዋል፡፡ በዓሉ በክርስትናችንና በእምነታችን ምን ያህል ጠንካራ እንደሆንን የምንገልጽበት ታላቅ በዓል በመሆኑ ምእመናን በአንድነት እና በፍቅር ሆነው ማክበር እንደሚገባቸው ጭምር አሳስበዋል፡፡

በዚሁ ታላቅ በዓል ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር ምክትል ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ “የጥምቀት በዓል የመልካችን ሰሌዳ የገጽታችን መገንቢያ ነው” ሲሉ ባስተላለፉት መልእክት ተናግረዋል፡፡



ክብርት ወ/ሮ አዳነች አቤቤ
የአ.አ.ከተማ አስተዳደር ም/ከንቲባ

የገጽታችን መገንቢያና የታሪካችን መንገሪያ የሆነውን የጥምቀት በዓል ማጉላትና መጠበቅ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ እንደሚጠበቅ ያነሱት ከንቲባዋ “የጥምቀት በዓል በዓለም

ቅርስነት ከተመዘገበ በኋላ ቅርሱ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የዓለም ቅርስ ሆኗል” ብለዋል፡፡

እንደ ከንቲባዋ ገለጻ ልዩ በህል፣ ቋንቋ፣ ማንነትና ቀለም ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሰባስበው በአንድ ላይ በዓሉን ማክበራቸው የጥምቀትን በዓል ልዩ ገጽታ አጎናጽፎታል፡፡ ነገር ግን ልዩነታችንን ምክንያት አድርገን ጫፍ ለጫፍ ቆመን ሀገር መገንባት፣ እግዚአብሔርን ማምለክና በዓላትን የጥምቀት በዓል አንድነታችን የሚጠናከርበት፣ ሰላማችን የሚረጋገጥበት እና ከፍቅር ስፍር የማንጎልበት በዓል ይሁን ሲሉም ከንቲባዋ ምኞታቸውን ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባና የጉራጌ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ለበርካታ ዓመታት የበዓለ ጥምቀት ማክበሪያ ቦታ ሆኖ ሲያገለግል የቆየው ጃንሜዳ የይዞታ ማርጋገጫ ካርታ ተሠርቶ ለቤተ ክርስቲያን እንዲሰጥ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድርን የጠየቁ ሲሆን ቦታውንም ለማልማትና ምቹ ለመድረግ ቤተ ክርስቲያን ዝግጁ መሆኗንም በዕለቱ አስታውቀዋል፡፡

# "ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች የሀገር መሠረቶች በመሆናቸው ተጠብቀው ለትውልድ ሊተላለፉ ይገባል''

***ብፁዕ አቡነ አብርሃም (የባሕ ርዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)***

ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች የሀገር መሠረቶች በመሆናቸው ጠብቆና ተንከባክቦ ለመጭው ትውልድ ማስተላለፍ እንደሚገባ የባሕ ርዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ገለጹ፡፡

ብፁዕነታቸው ይህንን የተናገሩት ‹‹የእመጓ ፍሬዎች›› በሚል ስያሜ በማኅበረ ቅዱሳን በቅዱሳት መካናትና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት ማስተባበሪያ ከእመጓ መጽሐፍ ሽያጭ በተገኘ ገንዘብ የተከናወኑ ሰባት ፕሮጀክቶች መጠናቀቃቸውን አስመልክቶ ጥር ፱ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በባሕ ርዳር ዩኔሰን ሆቴል በተዘጋጀው መርሐ ግብር ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልእክት ነው፡፡

የገዳማትን ችግር ለመፍታት ቤተ ክርስቲያንን ብቻ ባለድርሻ ማድረግ ተገቢ እንዳልሆነ ያነሡት ብፁዕነታቸው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያናቸው በእርጅናና በልዩ ልዩ ምክንያቶች የፈረሱ ገዳማት እንዲታደሱና የዕለት ጉርስ የሌላቸው ቀለብ አግኝተው የተጠናከረ ገዳማዊ ሕይወት እንዲመሩ መሥራት እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

ብፁዕነታቸው አያይዘውም ማኅበረ ቅዱሳን በገዳማት ላይ እየሠራ ያለው መልካም ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አሳስበው "ከዚህ በፊት ብዙ ሠርቷል፤ ብዙም እየሠራ ነው፤ወደፊትም ብዙ እንደሚሠራ እናምናለን›› ብለዋል፡፡

በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የአማራ ክልል ደራስያን ማኅበር ፕሬዚዳንት ሊቀ ኅሩያን በላይ መኰንን "ፈለገ ጥበብ ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ የመጀመሪያ መጽሐፋቸውን በስጦታ በመለገስ የኢኮኖሚና የመሠረተ ልማት ችግር ያለባቸው ገዳማት እንዲረዱበት ማድረጋቸው የሚያስመሰግንና ለሌሎችም ትምህርት የሚሆን ነው" ያሉ ሲሆን መጽሐፉ እጅግ ተነባቢ በመሆኑ ከንባብ ባህል ርቆ የቆየውን ትውልድ ወደ ንባብ ባህል እንዲመለስ ያደረገ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

በማኅበረ ቅዱሳን የቅዱሳት መካናት መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት ማስተባበሪያ ም/ኃላፊ ዲ/ን አንድነት ተፈራ በመርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ባቀረቡት ሪፖርት የአብነት ትምህርት ቤቶች መምህራንና ተማሪዎቻቸው እንዲሁም ገዳማዊያን ገዳማት ማንኛውም ዜጋ ከመንግሥት የሚያገኘውን ማኅበራዊ አገልግሎት እያገኙ ባለመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን አስተባብራ የማኅበራዊ አገልግሎት ተቋማትንና መሠረተ ልማቶችን ተደራሽ ታደርጋለች ብለዋል፡፡

የእመጓ መጽሐፍ ደራሲ ፈለገ ጥበብ ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ በዕለቱ ባስታለፉት መልእክት አብዛኛው የቱሪስት መዳረሻዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀብቶች እንደሆኑ አስረድተው እነዚህ የቱሪስት መዳረሻዎች የትውልዱን ሞራል ከመገንባት ባሻገር መንፈሳዊ ርካታን የሚሰጡ ቦታዎች ናቸው ካሉ በኋላ የገዳማቱን ገቢ በመጨመር ራሳቸውን የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ መላኩ አላምረው በበኩላቸው በሀገራችን በአብዛኛው ለቱሪስት መስህብነት የሚያገለግሉት ጥንታውያን ገዳማት መሆናቸውን ጠቁመው በአሁኑ ሰዓት የጎብኝዎች ቁጥር እንዲጨምርና ገዳማቱ በገቢ ራሳቸውን እንዲችሉ የማድረግ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡





# ዘመኑን መዋጀት ተገቢ ነው

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በአደባባይ ከምታከብራቸው በዓላት ውስጥ አንዱ የጥምቀት በዓል ነው። እጅግ በርካታ ቁጥር ያለው ምእመን የሚሰበሰብበት፣ የተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶች የሚከወኑበት ከዋዜማው (ከከተራው) ጀምሮ እስከ ዕለቱ የጥምቀት በዓል ድረስ አገልግሎቱ በሰፊው የሚሰጥ ከሌሎቹ የቤተ ክርስቲያን በዓላት ሁሉ ለየት ባለ ሁኔታ የሚከበር በዓላችን ነው። ታቦታት ከመንበረ ክብራቸው፣ ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ወጥተው ወደ ተዘጋጀላቸው ማደሪያ በመሄድ የሚከበር ታላቅ በዓላችን ነው።

የጥምቀት በዓል ምእመናን በብዛት የሚገኙበትና የሚከበር ብቻ ሳይሆን በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎች (ቱሪስቶች) የሚታደሙበት ታላቅ የአደባባይ በዓላችን ጭምርም ነው። ይህ ሕዝብ በብዛት የሚሳተፍበት ታላቅ በዓል ሃይማኖታዊ ዕሴቱን፣ ባሕላዊ ወጉን በጠበቀ መልኩ ሲከናወን መቆየቱ ዓለም አቀፍ ትኩረትን በመሳቡ በዓለም የማይዳሰሱ ቅርሶች ለመመዝገብ የበቃ እንዲሁም ለኢትየጵያውያን በተለይም ለኢትጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ጭምር ታላቅ ኩራትም ነው።

ይህ ብዙ ሕዝብ የሚሳተፍበት የአደባባይ በዓል (ጥምቀት) በተለይ የዚህ ዓመት የጥምቀት በዓል የተለየ የሚያደርገው በዓለም አቀፍ ደረጃ በፍጥነት እየተሰራጨ ፣በተለይም በአሁኑ ወቅት ደግሞ መልኩን ቀይሮ እና እጅግ የከፋ ሆኖ በመጣው የኮረና ወረርሺኝ ወቅት መሆኑ ነው። ይህ ዘር፣ ሃይማኖት እና ቀለምን ሳይለይ ብዙዎችን እየገደለ ያለው ዓለም አቀፍ በሽታ ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ተዳሮት ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል። ቤተ ክርስቲያን ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ከትላንት ዛሬ የተሻለ ቢሆንም ወደ ትላንቱ እንዳንመለስና ቤተ ክርስቲያን ዳግም እንዳትዘጋ በዚህ የአደባባይ በዓላችን ላይ ወቅቱን የዋጀ ትልቅ ሥራ መሥራት አስፈላጊ ነው።

የጥምቀት በዓል በቤተ መቅደስ እና በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ከሚከናወነው መንፈሳዊ አገልግሎት በተለየ መልኩ በአደባባይ የሚከበርና በርካታ ሕዝብ የሚሳተፍበት እንደመሆኑ መጠን የቫይረሱ ስርጭት እንዳያባብሰው እጅግ ጥንቃቄን ያሻል። ቤተ ክርስቲያን ቅድሚያ ሰጥታ ከምታስተምረው፣ ከምትመክረው እንዲሁም ከምትከውን የጾም የጸሎትና የምሕላ አገልግሎት ጎን ለጎን ቫይረሱን ለመግታት የሚወሰዱ እንቅስቃሴዎችም ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ወቅት ነውና ሊታሰብበት ይገባል።

የኮቪድ-፲፱ ወረርሺኝ መከሰት በዓለም አቀፍ ደረጃ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ላይ ዘርፈ ብዙ ተጽእኖ አስከትሏል። ይህ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ሀገራችን ኢትዮጵያን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናችንን በእጅጉ ጎድቶ አልፎአል አሁንም እየጎዳ ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚከበሩ ታላላቅ በዓላት ላይ ለመታደም ከመላው ዓለም የሚመጡ ጉብኚዎች ቁጥር በእጅጉ እንዲቀንስ ምክንያት የሆነው ወረርሽኝ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። ይህ አሉታዊ ተጽዕኖ በዚህ እንዳይቀጥል የቤተ ክርስቲያን ልጆች ከምእመናን እስከ ቅዱስ ሲኖዶስ በአንድነት ሊሠሩ ይገባል።

ሕዝብ በብዛት በሚገኝበት በዚህ የጥምቀት በዓል ላይ የኮቪድ-፲፱ ወረርሺኝ እንዳይስፋፋ የሚደረገው ቅድመ ጥንቃቄ ከግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ሊሠራበት ይገባል። ከዓሉ ዝግጅት ጎን ለጎን የቫይረሱን ስርጭት መከላከል ስለሚቻልበትና ስለሚወሰደው ቅድመ ጥንቃቄ አብሮ

ትምህርት ሊሰጥ ይገባል:: ኮቪድ ወደ ሀገራችን በገባ የመጀመሪያዎቹ ወራት አብያተ ክርስቲያናት እንዲዘጉ ብሎም ምእመናን እንዳይሰበሰቡ እስከ ማድረግ መድረሱ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው:: ይህ ነገ ተመልሶ እንዳይመጣ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ አጥብቃ ልትሠራበት ምእመናንን ልታነቃበትና ራሳቸውንና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ማዳን የሚችሉበትን ትምህርት ልታስተምር ይገባታል::

ዓለም አሁን እያስተናገደች ባለችው በዚህ አደገኛ ወረርሺኝ ተጠቂው ሰው እና የሰው ልጅ ብቻ ነው:: በዚህ ወረርሺኝ ሳቢያ ብዙዎች በጅምላ ሞተዋል፤ ዛሬም ለቁጥር የሚያታክት የሰው ልጅ እየተቀጠፈ ያለበት ጊዜ ነውና ምእመናን ከቤተ ክርስቲያን አባቶች እና አገልጋዮች እንዲሁም ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመናበብ መሥራት ይጠበቅባቸዋል:: ቤተ ክርስቲያን የምትኖረው ምእመናን ሲኖሩ ነውና የሰዎች ደኅንነት ሰፊ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: በመሆኑም ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ተከታዮቿ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል::

ከጾም፣ ከጸሎቱ እና ከምህላው ጎን ለጎን የጤና ባለሙያዎች፣ የመንግሥት አካላት የሚሰጡትን ምክር ተግባራዊ ማድረግ ከሁሉም የቤተ ክርስቲያኒቱ አካላት ይጠበቃል:: በዓሉ የአደባባይ እና ብዙ ሕዝብ የሚሳተፍበት እንደመሆኑ በሽታውን ሊያስተላልፉ የሚችሉ እና ስርጭቱን የሚጨምሩ ድርጊቶችን ከማድረግ መቆጠብ እጅግ አስፈላጊ ነው:: በበዓሉ ላይ ቤተ ክርስቲያኒቱም ሆነ ሌሎች የመንግሥት አካላት የሚሰጡትን መመሪያ መተግበር ከእያንዳንዱ ክርስቲያንም የሚጠበቅ ነው::

ክርስቲያን እንደመሆናችን መንፈሳዊውን መፍትሔ በጸሎትና በምህላ እየተጋን ቫይረሱ የሚሰራጭበትን መንገድ ለማጥበብ አካላዊ ርቀትን መጠበቅ፣ ጭምብል ማጥለቅና ንጽሕናን መጠበቅ ከሁላችን ይጠበቃል:: ይህን ለማስፈጸም በየደረጃው የሚገኙ የተለያዩ አካላትንም መስማት እና መታዘዝ ይልቁንም ለክርስቲያን ተገቢ ነው:: የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሳይታጎል ይቀጥል ዘንድ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል:: የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ወደ ቀደመ ስፍራቸው እንዲመለሱ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ዛሬ ላይ አጥብቀው ሊሠሩ ይገባል::

በየጊዜው መልኩን እየለወጠ የመጣውን ወረርሺኝ እንደ አመጣጡ ተቀብሎ ለጊዜው የሚያስፈልገውን ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ለዚህም የቤተ ክርስቲያን ልጆች ንቁ ተሳታፊ መሆን ይጠበቅባቸዋል:: ይህን ማድረግ በራሳቸውም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ላይ ከሚደርሰው ፈተና መታደግ ነውና:: ሥርዓቱ ሳይቋረጥ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲቀጥል ምእመኑ የሚተላለፉትን መመሪያዎችንም ሆነ ትእዛዞች ሰምቶ ሊተገብር ይገባል:: ምእመኑ ራሱ ከመጠንቀቅ አልፎ አንዱ ለሌላው አስተማሪ እና መካሪ ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል::

የአደባባይ በዓላችን ክብሩን ጠብቆ ሁሉም የሚመለከተው አካል የድርሻውን ሊወጣ ይገባል:: ዘመኑን መዋጀት እና በጥንቃቄ መጓዝ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ ኃላፊነት ነው:: በአጠቃላይ ከጸሎት ጋር ጥንቃቄ ያስፈልጋል እንላለን::

# በጥምቀታችን እንድመቅበት በተሰጠን እንወቅበት

በዲ/ን አሻግሬ አምጤ

ኢትዮጵያውያን በፍቅር አብረው እንዳይኖሩ የሚያደርጋቸውን ስስ ብልት እየፈለጉ ሲያጋጩ የነበሩ አሁንም በጥፋታቸው የቀጠሉ አካላት በመንግሥት መዋቅርም፣ በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ውስጥ መኖራቸው አገር ያወቀው፣ ፀሐይ የሞቀው እውነታ ነው። ከመገለጫዎች አንዱም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የአደባባይ በዓላት እንዳይከበሩ ምክንያት እየፈለጉ ማስተጓጎል፣ የሚደርስባቸውን መከራም ጆሮ ዳባልበስ ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን አድሎ የሚታይበት እኩይ ድርጊት እንዲታረም እና ወጥነት ያለው ሥርዓት እንዲሰፍን ስትጠይቅ ቆይታለች። የቅድመ አደጋ ስጋት ክትትልና መከላከል ሥርዓት እንዲዘረጋ እስከ መወሰን የደረሰችውም ለዚህ ነበር። ቅዱስ ፓትርያርኩ በጥቅምቱ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በተከፈተበት ወቅት "ቤተ ክርስቲያናችንን ለማዳን ክርስቲያኖች ራሳችንን እናዘጋጅ!" በማለት የተናገሩትም በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው መከራ እየተባባሰ በመቀጠሉ ነው።

ባለፈው ዓመት ማለትም በ፳፻፲፪ ዓ.ም ዩኒስኮ በዓለም ከማይዳሰሱ ቅርሶች አንዱ እንዲሆን ያደረገው የጥምቀት በዓል የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ የሚገልጥ ቢሆንም የኢትዮጵያውያን ሁሉ መለያችን መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። የቤተ ክርስቲያን የሆነው ነገር ሁሉ የኢትዮጵያውያን ሁሉ መሆኑን ከተረዳን መጠበቅ የሚኖርብንም ሁላችን መሆናችንን መገንዘብ ይኖርብናል። ተባብረን መጠበቅ የሚገባን የኦርቶዶክሳውያንን መገለጫ ብቻ ነው እያልን አለመሆናችንም መታወቅ ይኖርበታል። በሃይማኖት ብንለያይም ያለችን አንድ አገር በመሆኗ ያላትን ሁሉ የመጠበቅ ኃላፊነትም ግዴታም ያለብን ኢትየጵያውያን በሙሉ ነን። የምንጠብቀው የራሳችን ሃይማኖት መገለጫ የሆነውን ብቻ ከሆነ የሌላው ሲወድም የማይገደን ከሆነ አገራችንን የልዩ ልዩ ባህል ባለቤት መሆኗን እየተቃወምን መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።

ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በፍቅር አብረው እየኖሩ የሃይማኖት በዓላቸውን በጋራ ሲያከብሩ መኖራቸው የሚታወቅ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአገራችንን ታሪክ የማይረዱ አንዳንድ አክራሪዎች ከራሳችን ውጭ የሆነውን ሁሉ ማየት አንፈልግም ቢሉም እውነታው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተከሠቶ በስጋት እንድንኖር እያደረገን እንዳለው አልነበረም። ሙስሊሞች የክርስቲያኖችን፣ ክርስቲያኖችም የሙስሊሞችን በዓላት በጋራ አክብረው አብረው በልተው ጠጥተው ደስታቸውን ሲገልጡ መኖራቸው ይታወቃል። በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች ተከባብረው ሲኖሩ እንጂ ተገፋፍተው የጎሪጥ ሲተያዩ አልኖሩም። ተባብረው በፍቅር ባይኖሩ አንድ ሆነው አገራቸውን ጠብቀው ማቆየት ባይቻላቸውም ነበር። መተባበሩም ከሙስሊሞች ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ቤተ እምነቶች ጋር ጭምር መሆን ይገባዋል። ኦርቶዶክሳውያንን ለማቃጠል የተለኮሰ እሳት ሌሎችንም ሲያቃጥል እያየን በመሆኑ መተባበር ግዴታችን ነው።

ዛሬም እንደጥንቱ አገራዊ አንድነታችንንና ሃይማኖታዊ ትብብራችንን የሚገልጥ ተግባር በሐረሪ ክርላዊ መንግሥት መፈጸሙን የክልሉ ኮሚንኬሽን ቢሮ ገልጧል። ጉዳዩንም "በሐረር የጥምቀትን በዓል ምክንያት በማድረግ የእስልምና እምነት ተከታዮች እና የሰላም ቤተሰቦች በአንድነት ታቦታት የሚያልፉባቸውን መንገዶች ማጽዳታቸውን" የክልሉ ኮሚንኬሽን ቢሮ በማኅበራዊ ገጹ አስታውቋል። በዓሉ ያለምንም የጸጥታ ችግር እንዲከበር እየተሠራ መሆኑንም ጨምሮ ነግሮናል ። እንዲህ ዓይነቱ በጎ ጅምር ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ባለፈው ዓመት የተፈጸመውን አሰቃቂ ተግባር አስታውሰን በዚህ ዓመት የሆነውን ስንሰማ ወደ ቀደመው የመከባበርና የመተሳሰብ ባህላችን እየተመለስን መሆኑን እንድንረዳ ያደርገናል።

የክልሉ መንግሥት ክርስቲያኖች በዓላቸውን እንዲያከብሩ ጥበቃ ከማድረግ አልፎ ታቦታቱ የሚያልፉባቸው

መስመሮች እንዲጸዱ የክልሉን ሙስሊም ወገኖቻችንን ማስተባበሩ የኢትዮጵያዊው እሴታችን መገለጫ ተግባር በመሆኑ ሊመሰገን ይገባል። ለኢትዮጵያውያን የሚያምርብንም እንዲህ ዓይነቱ መደጋገፍ እንጂ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት መጠላለፉ አይደለም። በአገራችን የክርስቲያኖች እና የሙስሊሞች ትብብር የዓለምን ሕዝብ ሲያስገርመው እንደኖረው ሁሉ ወደ ፊትም መቀጠል የሚኖርበት የተሳሳተው እየታረመ፣ የተዛነፈው እየተስተካከለ፣ የተጣመመው እየተቃና ነው። ትልቁን ነገር እያጎሉ የልዩነት አጥር ከመሥራት እና በለው ፣ፍለጠው ከማለት ይልቅ በሚያስተሳስረን ጉዳይ አብረን እየሠራን በልዩነታችን ተከባብረን መኖር ሁላችንንም ይጠቅመናል።

እንዲህ ዓይነቱ በጎ ተግባር በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥትና በአንዳንድ የኦሮምያ አካባቢዎችም ቢደገም አገራችን ሰላም ውላ ታድራለች። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአደባባይ በዓላት ከሆኑት አንዱ የሆነው መስቀል ተከብሮ በማያውቅባቸው በዓረብ አገራት በሰላም ሲከበር በአንዳንድ የኦሮምያ አካባቢዎች ሳይከበር መቅረቱን የምናስታውሰው ነው። በያዝነው ፳፻፲፫ ዓ.ም በኦሮምያ ክልላዊ መንግሥት በሚገኙ ቢሸፍቱና አዳማ ክርስቲያኖች መስቀልን እንዳያከብሩ በመከልከላቸው ክርስቲያኖች ብቻ ሳንሆን ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በልቅሶ፣ በመከራ፣ በኀዘን አሳልፈነዋል። በዚህም ከክርስቲያኖች በላይ የጎዳው ከልካዮችን መሆኑን መረዳት ይገባል። በአገራችን የዐደባባይ በዓላት እስከ ዘመናችን ድረስ በደስታና በምስጋና ሲከበሩ ጠብቀው ማቆየት ባልተቻላቸውም ነበር። መተባበሩም ከሙስሊሞች ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ቤተ እምነቶች ጋር ጭምር መሆን ይገባዋል። ኦርቶዶክሳውያንን ለማቃጠል የተለኮሰ እሳት ሌሎችንም ሲያቃጥል እያየን በመሆኑ መተባበር ግዴታችን ነው።

ዛሬም እንደጥንቱ አገራዊ አንድነታችንንና ሃይማኖታዊ ትብብራችንን የሚገልጥ ተግባር በሐረሪ ክርላዊ መንግሥት መፈጸሙን የክልሉ ኮሚንኬሽን ቢሮ ገልጧል። ጉዳዩንም "በሐረር የጥምቀትን በዓል ምክንያት በማድረግ የእስልምና እምነት ተከታዮች እና የሰላም ቤተሰቦች በአንድነት ታቦታት የሚያልፉባቸውን መንገዶች ማጽዳታቸውን" የክልሉ ኮሚንኬሽን ቢሮ በማኅበራዊ ገጹ አስታውቋል። በዓሉ ያለምንም የጸጥታ ችግር እንዲከበር እየተሠራ መሆኑንም ጨምሮ ነግሮናል ። እንዲህ ዓይነቱ በጎ ጅምር ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ባለፈው ዓመት የተፈጸመውን አሰቃቂ ተግባር አስታውሰን በዚህ ዓመት ሊተገበር የታሰበውን ስንሰማ ወደ ቀደመው የመከባበርና የመተሳሰብ ባህላችን እየተመለስን መሆኑን እንድንረዳ ያደርገናል።

የክልሉ መንግሥት ክርስቲያኖች በዓላቸውን እንዲያከብሩ ጥበቃ ከማድረግ አልፎ ታቦታቱ የሚያልፉባቸው መስመሮች እንዲጸዱ የክልሉን ሙስሊም ወገኖቻችንን ማስተባበሩ የኢትዮጵያዊው እሴታችን መገለጫ ተግባር በመሆኑ ሊመሰገን ይገባል። ለኢትዮጵያውያን የሚያምርብንም እንዲህ ዓይነቱ መደጋገፍ እንጂ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት መጠላለፉ አይደለም። በአገራችን የክርስቲያኖች እና የሙስሊሞች ትብብር የዓለምን ሕዝብ ሲያስገርመው እንደኖረው ሁሉ ወደ ፊትም መቀጠል የሚኖርበት የተሳሳተው እየታረመ፣ የተዛነፈው እየተስተካከለ፣ የተጣመመው እየተቃና ሲሄድ ብቻ ነው። ትንሿን ነገር እያጎሉ የልዩነት አጥር ከመሥራት እና በለው ፍለጠው በማለት ይልቅ በሚያስተባብረን ጉዳይ አብረን እየሠራን ልዩነታችንን አክብረን መኖር ሁላችንንም ይጠቅመናል።

እንዲህ ዓይነቱ በጎ ተግባር በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥትና በአንዳንድ የኦሮምያ አካባቢዎችም ቢደገም አገራችን ሰላም ውላ ታድራለች። በአገራችን የዐደባባይ በዓላት እስከ ዘመናችን ድረስ በደስታና በምስጋና ሲከበሩ መኖራቸውን ታሪክ ይነግረናል። እኛም ደርሰን አይተናል። ዜጎችን ሁሉ ያለ አድልኦ አስተዳድራለሁ የሚል መንግሥት ባለበት አገር ክርስቲያኖች የዓደባባይ በዓላትን እንዳያከብሩ ተከልክለው በኀዘን እንዲያሳልፉ ሲደረግ የቆየውን ሊያስተካክል የሚችል በጎ ጅምር በመሆኑ በሌሎች አካባቢዎችም መደገም ይኖርበታል።

እስከ አሁን ሲፈጸም የነበረ እኩይ ድርጊት እንዳይደገም መሥራትና የሐረሪ ክልላዊ መንግሥት የፈጸመውን አርአያ ማድረግ ለሰላምና መረጋጋት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ አንድንድ አካላት ሌሎችን ለማሳነስና ለማዋረድ የሚፈጽሙት ተግባርና የሚናገሩት ቃል ሊያጠቋቸው ከፈለጓቸው ወገኖች የበለጠ ራሳቸውን ሊያሳንሳቸው እንደሚችል የሚከተለውን ታሪክ አንብበን እንረዳ፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ በሥልጣን እየተሻኮቱ ብዙ ጊዜ ለጦርነት መጋበዛቸውን የምናውቀው ነው፡፡ በመሆኑም ሊቃውንቱ እንዴት የአንድ አገር ሕዝብ እርስ በርሱ ሲጫረስ ዝም ብለን እናያለን ብለው ለማስታረቅ ተነሡ፡፡ አለቃ ምላት፣ አለቃ ሥነ ጊዮስጊስ፣ መምህር አካለ ወልድ ሁለቱን ወገኖች ለማስማማት ካሸማገሉ ሊቃውንት የሚጠቀሱ ነበሩ፡፡

**የክልሉ መንግሥት ክርስቲያኖች በዓላቸውን እንዲያከብሩ ጥበቃ ከማድረግ አልፎ ታቦታቱ የሚያልፉባቸው መስመሮች እንዲጸዱ የክልሉን ሙስሊም ወገኖቻችንን ማስተባበሩ የኢትዮጵያዊው እሴታችን መገለጫ ተግባር በመሆኑ ሊመሰገን ይገባል። ለኢትዮጵያውያን የሚያምርብንም እንዲህ ዓይነቱ መደጋገፍ እንጂ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት መጠላለፉ አይደለም።**

በአንድ ወቅት ዐፄ ዮሐንስን ለመማለድ ትግራይ ሔደው ከነበሩ ሊቃውንት አንዱ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ከንጉሡ ዘንድ ቀርበው በነረበት ሰዓት በንጉሥ ምኒልክ የተበሳጩት ዐፄ ዮሐንስ ደብዳቤ ሊልኩባቸው ፈልገው ጸሐፊያቸውን "ይድረስ ከመርድዕ አዝማች ምኒልክ ብለህ ጻፍ" ይላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ "ጃንሆይ እንደዚህ ብለው አይጻፉ" ይላሉ፡፡ ንጉሠ ነገሥቱም "እኮ ለምን" በማለት መልሰው ይጠይቃሉ፡፡ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስም "ምኒልክ መርድዕ አዝማች ከተባሉ እርስዎ ንጉሠ ነገሥት መባልዎ ቀርቶ ዝቅ ብለው ንጉሥ መባልዎ አይደለምን? ምኒልክ ንጉሥ በመሆናቸው እርስዎ ንጉሠ ነገሥት ተባሉ" ሲሏቸው ንጉሡም የሊቅ ቃል አክባሪ ስለነበሩ"ይህ ነገር እውነት ነው፤ በል ይድረስ ከንጉሥ ምኒልክ ብለህ ጻፍ" ብለው አሳባቸውን አስተካከሉ፡፡ ሁለቱም ቅን መሪዎች ስለነበሩ የሊቃውንቱን አሳብ ተቀብለው ታረቁ፡፡

የዘመናችን ባለ ሥናጣናትም ሌሎችን ለማንኳሰስ ብለው የሚጠቀሙበት ተግባር የራሳቸውን ክብር ዝቅ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ሚዛናዊ አስተሳሰብ የሌላቸው መሆኑን ስለሚያሳይባቸው ስሕተታቸውን ለማረም እንጂ በስሕተት ላይ ስሕተት ለመጨመር መትጋት አይፈልጉም፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በመገዳደር 'ሰባሁ እረዱኝ' ማለት መሆኑን ብቻ ሳይሆን ሥልጣናቸውን እንደሚያሳጣም መገንዘብ ኖርባቸዋል፡፡

ከግጭትም የከሰረ እንጂ ያተረፈ ባለመኖሩ የሚፈጸመው ሁሉ ሚዛን የጠበቀ ይሆን ዘንድ እናሳስባለን፡፡ ለሁላችን የሚበጀውን ከመፈጸም ይልቅ እናንተ እየሞታችሁ ቻሉት እኛን ግን ምንም አይንካን ከሚል አሳብ በመውጣት ሁሉን በእኩል ሚዛን ማየት መለመድ የሚገባው ተግባር ነው፡፡

የሆሣዕና ከተማ ኦርቶዶክሳውያን ከ፴ ዓመታት በላይ አምልኮ ሲፈጽሙበት የኖረውን የጥምቀትና የመስቀል በዓል ማክበሪያ ይዞታቸውን በከተማ አስተዳደሩ መነጠቃቸውን በተደጋጋሚ ስንሰማና ስንዘግብ መቆየታችን ይታወቃል፡፡ ሆሣዕናዎችም ሐረሪዎችን አብነት ቢያደርጉ የሥልጣን ዘመናቸው ጭምር ይረዝማል እንጅ አያጥርም፡፡ ሰላም ሲሰፍን፣ አካባቢውን በመገንዘብ ጭር ሲል አልወድም ማለት ከግጭት የሚያተርፉ አካላት ሥልጣን ላይ ለመቆየት መፈለጋቸውን እንደሚያሳይ መረዳት ይገባል፡፡ ግጭት ተቀስቅሶ አገር እንዲበጠበጥ የሚሠሩ አካላት ሁል ጊዜ ተረጋግቶ የሚኖረውን ሕዝብ ሲያጨፋጭፉ ትልቅ ሥራ የሠሩ ይመስላቸዋል፡፡ እንዲህ አይነት ሰዎች መደበቂያቸው ሃይማኖት ወይም ጎሳ ነው፡፡ ዓላማቸው ባይሳካ እንኳ ሕዝብ ጎራ ለይቶ ደም ሲፋሰስ በሰው ኀዘን ይደሰታሉ ይህ ግን ለአገራችን አይበጃትም፡፡

✝ ✝ ✝

# ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር) ሊቀ ጳጳስ ከ፲፱፻፵፫-፳፻፲ ዓ.ም



ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር) ሊቀ ጳጳስ

***ክፍል አንድ***

**በመጽሐፈ ሲራክ**

***የመጀመሪያውን ክፍል ከተወለዱበት ጀምሮ በቅዱስ ሲኖዶስ መልካም ፈቃድ በጸሎትና በቡራኬ እንዲቆዩ እስከተወሰነበት ጥቅምት ወር ፳፻፲ ዓ.ም ድረስ ያለውን የሕይወታቸውን ገጽ ወይም ዜና ሕይወት እንደሚከተለው አቅርበነዋል መልካም ንባብ፦***

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ፦ ከልጅነት እስከ ማዕረገ ጵጵስና

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር) ሊቀ ጳጳስ በመጀመሪያ ስማቸው ሣህለ ማርያም ከአባታቸው ከመምህር ቀሲስ ገብረ ሕይወት ወልደ ሐዋርያት እና ከእናታቸው ወ/ሮ ብርነሽ ቸኮል በቀድሞ ወሎ ክፍለ ሀገር በዋግ ሕምራ አውራጃ ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ.ም ተወለዱ።

ከካህን ቤተሰብ የተገኙት ብፁዕነታቸው ከፊደል ጀምሮ እስከ ግብረ ዲቁና ከዚያም እስከ ቅስና ያሉትን የቤተ ክርስቲያን ሙያዎች ከወላጅ አባታቸው ከመምህር ቀሲስ ገብረ ሕይወት እና ከአደጉበት አካባቢ ከነበሩ መምህራን ጀምረው ዐሥር ዓመት ሲሞላቸው ከቤተሰባቸው ተለይተው እና ከአካባቢያቸው ርቀው ወደ ዛታ ከተማ በመሔድ ከክርስትና አባታቸው ከመምህር ገብረ ጻድቅ ንባብና ዳዊት ፣ መዝገበ ቅዳሴን እስከ ሰዓታት ተምረዋል።

***ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ላለፉት ፵ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን በቅንነት አገልግለዋል። መንፈሳዊ አገልግሎታቸው በሀገር ውስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም ከሀገር ውጪም እንጂ። በትምህርት ረገድም በሀገር ውስጥ እና በውጭው ዓለም ብዙ ዕውቀትን ገብይተዋል። በተለይ የአብነት ትምህርትን በተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውረው በሀገሪቱ ውስጥ አሉ ከሚባሉ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ቀስመዋል። የአብነት ትምህርት ለመማር ወጥተው ወርደዋል፣ የትውልድ ሀገራቸውን ትተው፣ ከውሻ ተከላክለው፣ ቁራሽ እንጀራ ለምነው፣ ደበሎ ለብሰው፣ ተርበው ተጠምተው ጸዋትወ መከራውን በመታገሥ ሁሉን በጸጋ ተቀብለዋል። ብዙ የሕይወት መሰናክሎችን አልፈው ለትልቅ ማዕረግ በቅተዋል።***

***የብፁዕነታቸውን የ፵ ዓመታት የሕይወት ጉዞ እና ሥራዎቻቸውን በሁለት ክፍል ለማቅረብ ወደድን***

በመቀጠል ወደ ደብረ ዘመዳ ቅድስት ድንግል ማርያም አንድነት ገዳምና ደብረ ማርያም መሐጎ ማርያም በመሄድ ከየኔታ ወልደ እግዚእ ተጨማሪ ትምህርቶችን የተማሩ ሲሆን በተለይ በቅድስና ሕይወታቸው ከሚታወቁት መምህር ኤልሳዕ ወልደ ገብርኤል ጸዋትወ ዜማ በሚገባ ተምረው አጠናቀዋል። በወቅቱም ከወሎ ክፍለ ሀገር እስከ አሰብ ድረስ ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከአቡነ ይስሐቅ የዲቁና ማዕረግ ተቀብለዋል። ከታላቁ ደብር ደብረ ሳሙኤል

ከሚገኙት ጺጋ ዘአብ ወልደ ኢየሱስ የውዳሴ ማርያምንና የዳዊትን ትርጓሜ ተምረው አጠናቀዋል።

ብፁዕነታቸው ለቅኔ ካላቸው ከፍተኛ ፍቅር እና ተሰጥዖ የተነሳ በዘመናቸው አሉ ከሚባሉ የቅኔ መምህራን ቅኔን ከነአገባቡ በተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውረው ተምረዋል። ወርጫት ቅዱስ መድኃኔ ዓለም ደብር ከሚገኙት አረጋዊ መምህር ከየኔታ ጥዑመ ልሳን አማራው፣ ከመምህር ውቤና እና ከየኔታ መኮንን በሚገባ ቅኔን ከነአገባቡ ተምረዋል። እንዲሁም በወሎ ክፍለ ሀገር በራያ ቆቦ ዞብል አደባባይ ኢየሱስ ከነበሩት ከታላቁ ምስክር ከሊቀ ኅሩያን ወልደ ሰንበት የቅኔንና የአገባብን ይትበሃል በሚገባ አጠናቀው በመምህርነት ተመርቀዋል። ከቅኔው ጎን ለጎን የቅዱስ ያሬድን ዜማ እና የአቋቋም ትምህርት ያላቸውን ጊዜ በሚገባ በመጠቀም ተምረዋል።

**የአብነት ትምህርት ለመማር ወጥተው ወርደዋል፣ የትውልድ ሀገራቸውን ትተው፣ ከውሻ ተከላክለው፣ ቁራሽ እንጀራ ለምነው፣ ደበሎ ለብሰው፣ ተርበው ተጠምተው ጸዋትወ መከራውን በመታገሥ ሁሉን በጸጋ ተቀብለዋል። ብዙ የሕይወት መሰናክሎችን አልፈው ለትልቅ ማዕረግ በቅተዋል።**

በአንድ ወቅት የሥጋ ዘመዳቸው በነበሩት ዋግ ሹም ወሰን ኃይሉ አማካኝነት ወደ አዲስ አበባ የመምጣት እድል አግኝተዋል። ብፁዕነታቸው ይህንን እድል በመጠቀምም በኮልፌ ሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ አዳሪ ትምህርት ቤት ተወዳድረው እና የተሰጠውን የቅኔ፣የዜማና የአቋቋም ፈተና በብቃት አልፈው አዳሪ ትምህርት ቤቱ የመግባት እድል አገኙ። በዚያም ከ፲፱፻፶፬ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፶፰ ዓ.ም ለአራት ዓመታት የብሉያት መጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርት የኔታ ገብረ ማርያም እና የኔታ ታመነ ከተባሉ የታወቁ መምህራን ዘንድ ተምረው በማጠናቀቅ በመምህርነት ተመርቀዋል።

ብፁዕነታቸው በምንኩስና የቅድስና ሕይወት ጉዞ የጀመሩትና ለታላቁ ማዕረግ እንዲደርሱ የእግዚአብሔር ጥሪ የደረሳቸው በ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ነው። በዚህ ዓመት ወደ ደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንድነት ገዳም በመሄድ በጻድቁ ቃል ኪዳንና በአበው መነኮሳት ፈቃድ መነኮሱ። በመቀጠልም መስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ.ም በጊዜው የወለጋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የቅስና እና የቁምስናን ማዕረግ ተቀብለዋል።

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር) ሊቀ ጳጳስ በልጅነታቸው በወልድያና በደሴ ከተማ የጀመሩትን ዘመናዊ ትምህርት ወደ አዲስ አበባ ከመጡም በኋላ በትጋት ቀጥለዋል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በኮልፌ ሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በማጠናቀቅ ወደ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ተዘዋውረው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በጥሩ ውጤት ጨርሰዋል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ በነበራት የውጭ ግኙኝነት መሠረት የውጭ ሀገር የትምህርት ዕድል ከተሰጣቸው ስድስት ተማሪዎች መካከል አንዱ በመሆን ወደ ሩሲያ መስኮብ የቀድሞው ፒተርስበርግ በኋላ ሌኒን ግራድ ለትምህርት ተላኩ። በሌኒን ግራድ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሚሰጠውን የአምስት ዓመት ትምህርት በከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ በሃይማኖተ አበው (ፓትሮሎጂ) የጥናት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በማዕረግ አጠናቀው ተመርቀዋል። ከዲግሪው በተጨማሪ በማስተር ኦፍ ዲቪኒቲ (Master of Divinity) በትምህርተ መለኮት ዲግሪ ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ አጠናቀው ተመርቀዋል። የማዕረግ ተመራቂ የነበሩት ብፁዕነታቸው በነበራቸው ከፍተኛ ውጤት ዩኒቨርስቲው ተጨማሪ የትምህርት ዕድል በመስጠት በነገረ ክርስቶስ የዶክትሬት ዲግሪ (PhD) ጥናታቸውን እንዲቀጥሉ አደረገ። ለዶክተሬት ትምህርት የሚያበቃቸውን መሥፈርት ለማሟላት Christology of non Chalchedonian Church በሚል ኬልቄዶንን

የማይቀበሉ ክርስቲያኖች ስለ ነገረ ክርስቶስ ፣ ስለ ምሥጢረ ሥላሴ፣ ስለ ነገረ ማርያም ፣ ስለ ምሥጢረ ቅዱስ ቍርባን ያላቸውን እምነትና ከምሥራቃውያን ኬልቄዶናውያን ጋር ያለውን ልዩነት የሚያስረዳ ከ፩፻፺፱ ገጽ በላይ የጥናት ጽሑፍ አቅርበዋል። በተጨማሪም የአንጾኪያና የእስክንድርያ ትምህርት ቤቶች አንድነታቸውንና የሚለያዩበትን መሠረታዊ ነጥብ ፻፴ ገጽ በማቅረብ የዶክትሬት ዲግሪ ትምህርታቸውን ለመቀጠል የሚያበቃቸውን መሥፈርት አሟልተው በትምህርተ ሥጋዌ (Christology) የዶክትሬት ኦፍ ቴዎሎጂ ዲግሪ ተቀብለዋል።

ብፁዕነታቸው ወደ ሰሜን አሜሪካም በመሄድ ከፕሪስተን ዩኒቨርሲቲ (Preston University) ማስተር ኦፍ ቴዎሎጂ ዲግሪ ተቀብለዋል። በዚሁ ዘመናዊ ትምህርት ጉዞ በከፍተኛ ውጤት የተቀበሏቸውን የዶክተሬት ዲግሪ ሞስኮና ኒዮርክ በሚገኙት የትምህርት ኮሚሽኖች ሰነድ ማረጋገጫ መሥፈርት መርምሮ አጽድቆላቸዋል። በነበራቸው ከፍተኛ የትምህርት ዝግጅትም በሰሜን አሜሪካና በሩሲያ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ መምህር ሆነው በመመደብ አገልግለዋል።

በ፲፱፻፸ ዓ.ም ሦስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለይፋዊ ጉብኝት እና ስብሰባ ሩሲያ በሔዱበት ጊዜ ‹‹ቤተ ክርስቲያንህ ትፈልግሃለች ወደ ሀገርህ መምጣት አለብህ›› በሚል አባታዊ ጥሪ ብፁዕነታቸውን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል። ብፁዕነታቸው ወደ ሀገር ቤት ከመጡ በኋላ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ዋና ጸሓፊ ፣የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የካህናት አስተዳደር መምሪያ እና መንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል። በዚህ ኃላፊነት ላይ እያሉም ጥር ፬ ቀን በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ዶ/ር አባ ኢያሱ ይባሉ የነበሩት ብፁዕ አባ ገብርኤል ተብለው የመንፈሳዊ ኮሌጅ ኤጲስ ቆጶስ (ዲን)፣ የድሬዳዋና የአካባቢው ኤጲስ ቆጶስ ተብለው ተሹመዋል።

ብፁዕነታቸው በቅዱስ ሲኖዶስ መልካም ፈቃድ በጸሎትና በቡራኬ እንዲቆዩ እስከተወሰበት ጥቅምት ፳፻፲፫ ዓ.ም ድረስ በሀገር ውስጥ እና በውጪው ዓለም ቤተ ክርስቲያን ባሰማራቻቸው ቦታዎች ሁሉ በርካታ መንፈሳዊ ሥራዎችን ሲሰሩ ቆይተዋል።

በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም የኤርትራ ክፍለ ሀገር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በመሆን ለሦስት ዓመታት አገልግለዋል። በ፲፱፻፸፮ ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመዘዋወር የትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ኀላፊ ሆነው በመስራት ላይ እያሉ የኤርትራ ሀገረ ስብከት ካህናት እና ምእመናን እንዲመለሱላቸው ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ወደ ኤርትራ ተመልሰው እስከ በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በመሆን አገልግለዋል። በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመመለስ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የበላይ ኀላፊ ሆነው ለአንድ ዓመት ከሦስት ወር አገልግለዋል። በነበራቸውም ቆይታ በሀገረ ስብከቱ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፣ ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ፣ ሰንበት ት/ቤት እንዲደራጅ ብዙ ጥረዋል።

ብፁዕነታቸው በውጭ ሀገር በነበራቸው መንፈሳዊ አገልግሎት በጥቅምት ፲፱፻፹፭ ዓ.ም በቅዱስ በሲኖዶስ ትእዛዝ ወደ ካሪቢያን ሀገራት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተመድበው በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል። ከዚያ ተመልሰውም በግንቦት ወር ፲፱፻፹፭ ዓ.ም ወደ ሰሜን ወሎ ወልዲያ ሀገረ ስብከት ተዛውረው ስድስት ወር ሐዋርያዊ አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተው ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ወደ ሀገረ ስብከቱ ሲመለሱ ብፁዕነታቸው ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል። በ፲፱፻፹፮ ዓ.ም በመንበረ ፓትርያርክ የሕዝብ ግንኙነትና የውጭ ጉዳይ ኀላፊ በመሆን ለአምስት ወራት እንዲሁም የምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በመሆን ለሦስት ዓመት ከአምስት ወር አገልግለዋል። ከ፲፱፻፺ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ፳፻፪ ዓ.ም ድረስ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ተመድበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ጥንታውያን ገዳማትን አስተዳድረዋል።

ብፁዕነታቸው እስከ ፳፻፫ ዓ.ም በሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለሦስት ዓመታት የትምህርት ቤቱ የበላይ ኀላፊ ሊቀ ጳጳስ በመሆንም አገልግለዋል።

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶር) ከኅዳር ወር ፳፻፫ ዓ.ም ጀምሮ በቅዱስ ሲኖዶስ መልካም ፈቃድ በጸሎትና በቡራኬ እንዲቆዩ እስከተወሰነበት እስከ ጥቅምት ፳፻፲፫ ዓ.ም ድረስ የሲዳማ፣ጌዴኦ አማሮና ቡርጂ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በመሆን ዘርፈ ብዙ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል።

# “የቤተ ክርስቲያኒቱን ችግር በዘላቂነት መፍታት ካልተቻለ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ላናገኝ እንችላለን”

*- ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጄ ብርሃኑ*

**በእህተ ሚካኤል**

**ክፍል ሁለት**

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ቃለ መጠይቅ የመጀመሪያ ክፍል ባለፈው እትማችን ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። በዚህ እትማችን ደግሞ ክፍል ሁለትን ይዘንላችሁ ቀርበናል። በጥሞና ትከታተሉ ዘንድ ግብዣችን ነው።***

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በቀጣይ በቃለ ወንጌል በእምነታቸው እንዲጸኑ በማድረግ በሀገረ ስብከቱ እንደ እቅድ የተያዘ ነገር አለ? እየተሠራ ነው?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጄ፦*** አዎን እነዚህን ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች በተለየ መልኩ ተይዞ እየተሠራ ነው። አደራጅቶ በሀገረ ስብከቱ የስብከተ ወንጌል ክፍል የሚመራ ቡድን/ልኡክ አለ ይህን ልኡክ፣ ማኅበራትን በማቀናጀት ሰፋፊ ጉባኤያትን እየሠራን ነው። በእቅድም ይዘን ለመሥራት እየተንቀሳቀስን ነው። አሁን በቅርቡም ከአዲስ አበባ ዘማርያን እና ሰባክያነ ወንጌልን በመጋበዝ በመቻራ ወረዳ ላይ ታላቅ ጉባኤ አዘጋጅተናል። በቀጣይም ከአብያተ ክርስቲያናት ሰበካ ጉባኤ ጋር በመነጋገር እንደዚህ ዓይነቱን የማጽናናት ሥራ በሌሎችም ወረዳዎች አጠናክረን የመቀጠል እቅድ ነው ያለን።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በቀጣይ ቤተ ክርስቲያን የሚቃጡባትን መሰል ጥቃቶች ለመመከት ምን ማድረግ አለባት?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጄ፦*** ስለ ቀጣይ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ስንነጋገር በመጀመሪያ ቅዱስ ሲኖዶስ ትልቅ ኃላፊነት አለበት ብለን እናስባለን። ምክንያቱም ቅዱስ



***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጄ ብርሃኑ  
ምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ***

ሲኖዶስ ከማናቸውም የቤተ ክርስቲያኒቱ የሥልጣን መዋቅር ትልቁና የመጨረሻው ሥልጣን ሰጪና ወሳኝ አካል ነውና። ቅዱስ ሲኖዶስ በተለያየ ጊዜ ከተለያዩ ሀገረ ስብከቶች ጥቃቶችን አስመልክቶ የቀረቡለትን ሪፖርቶች በመረጃ በመያዝ ከሚመለከታቸው የመንግሥት የጸጥታ አካላት ጋር ቀርቦ በመነጋገር እነዚህ ችግሮች መስመር የሚይዙበትን መፍትሔ በማምጣት መመሪያዎችን በተዋረድ ወደታች ሊያወርድልን ይገባል።

ከዚህ ባሻገር ለምሳሌ እንደ ምዕራብ ሐረርጌ ፤እንደ ሀገረ ስብከታችን ደግሞ በሀገረ ስብከታችን ካሉት የዞን

የመንግሥት አካላት፤ የወረዳ የመንግሥት አካላት እንዲሁም የቀበሌ መስተዳደሮች አጠቃላይ የመንግሥት መዋቅር ጋር የቤተ ክርስቲያን ኀላፊዎች ተቀራርበው በመሥራት ችግሩ እንዲፈታ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ምክንያቱም ጥቃት እየደረሰበት ያለው ክፍል ከሌላ ዓለም የመጣ ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ነው። ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ደግሞ በየትኛውም ቦታ የመኖር ፣የመሥራት፣ ሀብት የማፍራት፣ የመንቀሳቀስ ሕገ መንግሥታዊ መብት እንዳለው ይታወቃል። መብቱ እንዲጠበቅለት የሚወጡ መመሪያዎችና ውሳኔዎች መሬት ላይ ወርዶ ሊሠራባቸው ይገባል።

በዚህ መንገድ የቤተ ክርስቲያኒቱን ችግር በዘላቂነት መፍታት ካልተቻለ እና ችግሩ የሚቀጥል ከሆነ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ላናገኝ እንችላለን። ቤተ ክርስቲያናችን የታሪክ ባለቤት ናት፤ ሀገርን ከነሙሉ ክብሩ፣ ከነቅርሱ ከነጀግንነቱ ያቆየች፣ የሀገር አንድነትን አጽንታ የያዘች ቤተ ክርስቲያን ናት፤ ስለዚህ ልትጠቃ ልትጎዳ አይገባም። በእኛ ቤተ ክርስቲያን በኩልም ከአጥቢያ ሰበካ ጉባኤ ጀምሮ እስከ ቅዱስ ሲኖዶስ ያለው መዋቅር መጀመሪያ መጠናከር አለበት፤ የእርስ በርስ የውስጥ መጠላለፍ ቀርቶ በጋራ በመሆን መዋቅሩን አጠናክረን ችግሩ ከመድረሱ በፊት የቅድመ መከላከል ሥራ መሠራት አለበት። ከዚህ በዋናው ማእከል ተቋቁሞ ከቅዱስ ሲኖዶሱ እስከ ታች ድረስ ወርዶ በእዝ ሠንሠለት በመዋቅር የተገናኘ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል ከዚህ በኋላ የምናንቀላፋበት ጊዜ ሊኖር አይገባም።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ፴፱ኛውን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ለመካፈል ሀገረ ስብከትዎን ወክለው ነው የመጡት ከጉባኤው ምን አገኙ?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጀ ፦*** ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በየዓመቱ የሚከናወን ነው። ይህ ፴፱ኛው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጥሩ ተሳትፎ ተደርጎበታል። ነገር ግን በዚህ በኮቪድ-፲፱ ወረርሺኝ ምክንያት ሰፊ የሆነ የጋራ ውይይት ለማድረግ አልተቻለም። ሆኖም ግን የየአህጉረ ስብከቱ ሪፖርት በሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ በኩል ነው የቀረበው እና የተነበበው። ለወደፊቱ እግዚአብሔር በሰላም ቢያደርስን ሰፊ ውይይት ያስፈልጋል። ለምሳሌ በዘንድሮው ዓለም አቀፍ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ በወቅታዊው የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የችግሩ ገፈት ቀማሾች በተለይ ችግሩ ያለባቸው ዞኖች፣ ሀገረ ስብከቶች የነበረባቸው ችግር ውይይት አልተደረገበትም ምክንያት ቢኖረውም። ችግሩ ሲነሳ፣ ለውይይት ሲቀርብ፣ ሲታወቅም ነው መፍትሔውም ሊገኝ የሚችለው።

የችግሩ ምንጭ እዚህ ጋር ነው፤ የችግሩ መንሥኤም ይህ ነው በመሆኑም መፍትሔው ደግሞ ይህ ነው ተብሎ በዝርዝር ሊቀመጥ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ቁጭ ብሎ መወያየት ያስፈልጋል። አሁን በኮቪድ ምክንያት ያንን ማድረግ አልተቻለም። ለቀጣዩ ግን ይህ እንዲሆን ሐሣቦች ከተሳታፊዎች ቀርበዋል። በአጠቃላይ እንደ ምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት በነበረው ስብሰባ ደስተኞች ነበርን፤ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ በሥራ አፈጻጸም ግምገማ ከምድባችን የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት አንደኛ ወጥተን መሸለማችን ነው እግዚአብሔር ይመስገን።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በ፴፱ኛው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከደረሱ ጥቃቶች ጋር ተያይዞ የተሰጠ መፍትሔ፤ እንደ አቅጣጫ የተቀመጠ ሐሳብ አለ?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጀ፦*** በጉባኤው ማጠቃለያ ላይ ባለ ፲፫ ነጥብ የአቋም መግለጫ አውጥተን ነው የተለያየነው። ይህ የአቋም መግለጫ ለቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ ቅዱስ ሲኖዶስ ከተነጋገረበት በኋላ ወስኖ ወደ ታች ይወርዳል ማለት ነው። ቅዱስ ሲኖዶስ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመቀራረብ እና አንድ ላይ በመሥራት

ሊፈታቸው የሚገባቸው ነጥቦች እዚህ የአቋም መግለጫ ላይ ተካተዋል፡፡ ስለዚህ እዚያ ላይ የቀረቡት ነጥቦች በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ከተወሰነ በኋላ ወደ ታች ይወርዳል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ትልቁ ነገር መወሰኑ ብቻ አይመስለኝም ከተወሰነ በኋላ ውሳኔው ተግባራዊ እንዲሆን መሬት የወረደ ሥራ መስራቱ ነው ቁም ነገሩ፡፡ ከዚህ ቀደም ብዙ ውሳኔዎች ተላልፈዋል፤ ነገር ግን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ክፍተት አለ፡፡ የተላለፉ ውሳኔዎችን ተከታትሎ የሚያስፈጽም አንድ ክፍል ሊቋቋም ይገባል ፡፡ አባቶች ይወስናሉ አባቶች የወሰኑትን ውሳኔ ማነው ተከታትሎ መሬት ላይ የሚያወርደው? ለምሳሌ ከመንግሥት አካል ጋር ተነጋግሮ ማለቅ ያለበት ጉዳይ ከሆነ ይህንን እስከመጨረሻው ጫፍ አድርሶ የሚያስወስን፤ የሚያስፈጽም አካል ያስፈልጋል፡፡

**ከዚህ ቀደም ብዙ ውሳኔዎች ተላልፈዋል፤ ነገር ግን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ክፍተት አለ፡፡ የተላለፉ ውሳኔዎችን ተከታትሎ የሚያስፈጽም አንድ ክፍል ሊቋቋም ይገባል፡፡ አባቶች ይወስናሉ አባቶች የወሰኑትን ውሳኔ ማነው ተከታትሎ መሬት ላይ የሚያወርደው?**

ውሳኔን የሚያስፈጽም አካል ካለ በየደረጃው የሚወርዱና የሚተላለፉ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን መፈጸም አለመፈጸማቸውን መከታተል ያስፈልጋል፡፡ ሁላችንም የሚተላለፉትን ውሳኔዎች ተግባራዊ እያደረግን ከመጣን ችግሮች ይፈታሉ፡፡ አሁን በጠቅላይ ቤተ ክህነት ደረጃ የሕዝብ ግኑኙነት መምሪያ ተቋቁሟል፡፡ በሀገረ ስብከትም ደረጃ እንዲቋቋም ደግሞ መመሪያ ተላልፏል በዚያ መሠረት አቋቁመናል፡፡ ቶሎ ቶሎ ግንኙነት በማድረግ ችግሮችን ለመፍታት የተቋቋመ መምሪያ ነው፡፡ ይህ መምሪያ ቢጠናከር ዘመኑ በሚጠይቀው ቴክኖሎጂ እየተጠቀምን መረጃ ለመቀባበል፣ለመለዋወጥ እና የተሻለ ሥራ ለመሥራት ያግዛል፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በመጨረሻ የሚያስተላልፉት ቀረ የሚሉትም ነገር ካለ ቢነግሩን?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጄ፦*** ይህች ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት፣ ጥንታዊት እና ታሪካዊት የሆነች በክርስቶስ ደም የተመሠረተች ቃል ኪዳን ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ‹‹የገሃነም ደጆች አይችሉአትም›› የተባለች ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ብዙዎች በየዘመናቱ እየተነሱ ቤተ ክርስቲያንን ሊያጠፉ ሞክረዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሰማዕትነትን ዘመን አሳልፋለች ገፊዎቿ የሉም ፣ ጠላቶችዋ ጠፍተዋል እስዋ ግን ሁሉን አሳልፋ ዛሬን አለች ወደፊትም ትኖራለች፡፡ በትንቢተ ናሆም ‹‹በመከራቸው ቀን ለሚታገሡ እግዚአብሔር ቸር ነው፤ እርሱን የሚፈሩትንም ያውቃቸዋል፡፡›› ናሆ ፩÷፯ ብሎ እንደተናገረው ቤተ ክርስቲያን መጠለያ ናት፤ እውነተኛ አምባችን ናት ፤ለጠላት አሳልፎ የማይሰጥ እውነተኛ እረኛ አባት እግዚአብሔርን የምናመልክባት ናት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡፡

ይህችን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ከውጭም ከውስጥም ጠላት በዝቶባታል፡፡ ስለዚህ ምእመናን በእምነታቸው ጸንተው እና ተግተው ቤተ ክርስቲያናቸውን ሊጠብቁ ይገባል፡፡ በቤተ

ክርስቲያን በኃላፊነት የተቀመጥን እረኞች በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንን የመጠበቅ፣ ምእመናንን የመጠበቅ ኀላፊነት አለብን። የእግዚአብሔር ሕዝቦች፣ ምእመናን ይበልጥ ወደ እርሱ እንድንቀርብ እግዚአብሔርን የረሱ፣ የዘነጉ በንስሓ እንዲመለሱ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የተለያዩ ነገሮችን ያመጣል፤ ስለዚህ መከራውና ፈተናው ለበጎ መሆኑን አምኖ በትዕግሥት ማለፍ ያስፈልጋል።

እግዚአብሔር እንደ ዳዊት ሊያነግሥ ሲፈልግ ጎልያድን ያህል ትልቅ መከራ ያመጣል። ምእመናንም በመጣው ፈተና ሊደነቁ አይገባም አምላካችን ክርስቶስም መከራ ተቀብሎአል ግን ዓለምን አሸንፏል፤ እኛም የክርስቶስ ልጆች ነን። ከፈተናው የምንማረውን ድክመታችንን አርመን፣ አስተካክለን እግዚአብሔርን የረሳንበት፤ እግዚአብሔርን ያላስታወስንበት፤ እግዚአብሔርን በሚገባ ያላገለገልንበትን ጊዜ በማሰብና ወደ ውስጣችን በመመልከት በንስሓ ወደ እግዚአብሔር ልንመለስ ይገባል።

ሌላው ሳላነሳው የማላልፈው እንደ ሀገረ ስብከታችን ስብከተ ወንጌልን፤ ምእመናንን ለማጠናከር በማሰብ ከሀገረ ስብከቱ የማኅበረ ቅዱሳን አሰበ ተፈሪ ማእከል ጋር በጋራ በመሆን ጥሩ የሆነ የአብነት /የአዳሪ ትምህርት ቤት/ ተገንብቶ አልቆ አሁን በቅርቡ የምርቃት ሥነ ሥርዓት ይካሄዳል። በዚህ ትምህርት ቤት ከገጠር ፣በዞኑ ውስጥ ካሉ በአካባቢ ያሉና አማርኛም ኦሮሚኛም የሚናገሩ ልጆችን በማሰባሰብ በየቋንቋው የሚያስተምሩ ዲያቆናትን ተተኪ ሰባኪያንን ለማፍራት የሚያስችል ሥልጠና ለመስጠት እየተዘጋጀን ነው።

ከዚያም ባሻገር ቀደም ሲል በሀገረ ስብከቱ G+2 ሁለ ገብ የሆነ ሕንጻ እያስገነባን ነው። በአሁኑ ሰዓት ሕንፃው ከ፹፭ በመቶ በላይ ስራው እየተጠናቀቀ ነው። የምድር ቤቱን ሙሉ በሙሉ ጨርሰናል። አንደኛና ሁለተኛ ፎቅ ደግሞ የሰባኪያን ማልጠኛ፣ ለሀገረ ስብከቱ ቢሮ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ይውላል። እነዚህ ነገሮች ተጠናክረው ከቀጠሉ የሀገረ ስብከቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በተሻለ ሁኔታ ለማስኬድ ምቹ ይሆናል።

በአጠቃላይ እረኛው የእረኝነቱን ተግባር በአግባቡ ከተወጣ፤ በጎችም የበግነታቸውን ከእረኞቻቸው ሥር ሳይጠፉ በእምነታቸው ሊጠነክሩ ይገባል። ከእረኛው እና ከበረቱ የወጣች በግ አንድም ለእርድ አንድም ለገበያ ነው ልትቀርብ የምትችለው። ምእመኑ በረቱን እናት ቤተ ክርስቲያንን ጥሎ ሊሄድ አይገባም። ከበረቱ ሊያስኮብልሉ የሚገፉፉ ብዙ መከራዎች፤ ብዙ ፈተናዎች ከውስጥም ከውጭም አሉ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚዎቿ ብዙ ናቸው። ስለዚህ ሁላችንም ነቅቶ በመጠበቅ፤ ተደራጅቶ በመሥራት፤ በውስጥ አሰራር እርስ በርስ የምንጋጭባቸውንና አለመግባባት ውስጥ የሚከቱንን ነገሮች ወደ ጎን ትተን ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን በቅንነት ልንቆም ይገባል።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጀ ይህን ቃለ መጠይቅ ስለሰጡን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጀ፦*** እኔም ለዚህ ቃለ መጠይቅ እንግዳ አድርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።

# የጥምቀት በዓል

በቀሲስ ዘክርስቶስ ፀጋዬ




የተወዳዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ሕፃናት! እንደምን ከርማችኋል? በእግዚአብሔር ቸርነት በሰላምና በጤና እንደቆያችሁን ተስፋ እናደርጋለን፤ ትምህርታችሁን በንቃት በመከታትል በመንፈሳዊም በሥጋዊም ዕውቀት ማደግ ይኖርባችኋልና በርቱ!

ልጆች! ዛሬ ስለጥምቀት በዓል እናስተምራችኋለንና በጥሞና ተከታተሉ!

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀበት ዕለት የምናከብረው በዓል የጥምቀት በዓል ይባላል፡፡ ጥምቀት የሚለው ቃል ‹‹ተጠምቀ፣ ተጠመቀ›› ካለው የግእዝ ግሥ የወጣ ሲሆን ትርጓሙም በውኃ ‹‹መነከር፣ በገዛ እጁ ወይም በሰው እጅ ሥርየት ወይንም ልጅነት ለማግኘት መጠመቅ›› ማለት ነው፡፡ (መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ገጽ ፫፻፪) ጥምቀት በተቀደሰ ውኃ መጠመቅ ማለት ነው፤ ይኸውም ቀሳውስት በጸሎት ሥርዓት ከቀደሱት በኋላ ምእመናንን (ክርስቲያኖችን) በተቀደሰው ውኃ ያጠምቋቸዋል፡፡ ካህናቱ ሕዝቡን ጸበል ከረጩ በኋላ ልዩ ልዩ ሥርዓቶች ይደረጋሉ፤ ከዚያም ታቦታቱ ከድንኳን ወጥተው ወደ የመጡበት ቤተ ክርስቲያን ይሔዳሉ፡፡ ‹‹ጥሩ ውኃንም ረጭባችኋለሁ፤ እናንተም ትጠራላችሁ›› (ሕዝ. ፴፮፥፳፭) ተብሎ እንደተነገረው፡፡ ውኃ ለሰው ልጆች በሙሉ አስፈላጊ ነው፤ ያለ ውኃ መኖር አይቻልም፡፡ ጥምቀትም ለሁሉም የሚያስፈልግ በመሆኑ ያለ ጥምቀት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይቻልም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ውኃ መልክ ያሳያል፤ መልክ ያለመልማል (ያጠራል)፡፡ ጥምቀትም መልክአ ነፍስን ያሳያል፤ መልክአ ነፍስን ያለመልማልና (ያጠራልና) ጌታችን በውኃ ተጠመቀ፡፡

በጥምቀት በዓል ጌታችን ወደ ዮርዳኖስ ሄዶ እንደተጠመቀ ለማስታወስ ጥር ፲ (ዐሥር) ቀን ሁሉም ታቦታት በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ ውኃ ወዳለበት ሥፍራ በመሔድ በድንኳን ውስጥ ያድራሉ፤ ይህም ዕለት ከተራ ይባላል፡፡ ከተራ የተባለው በአካባቢው ያለው ውኃ እንዳይፈስ ተገድቦ ሕዝቡ እንዲጠመቅበት ስለሚዘጋጅ ነው፡፡ ታቦታቱ ወደ ድንኳኑ ከገቡ በኋላ ሌሊቱን ካህናቱ ሲያመሰግኑ፣ ሲዘምሩና ሲቀድሱ እንዲሁም በዓሉን የተመለከተ ትምህርት ለሕዝቡ ሲያስተምሩ ያድራሉ፡፡ ከጥዋቱ ፲፪ (ዐሥራ ሁለት) ሰዓት ጀምሮ ደግሞ ወደመጠመቂያው ውኃ በመሄድ በውኃው ላይ ጸሎት ከተደረገ እና ከተባረከ በኋላ

የተሰበሰበው ሕዝብ በተጸለየበት ጸበል ይረጫል፡፡

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት ምክንያት እርሱ ተጠምቆ ለነፍሳችን ድኅነት መሆኑን ሊያሳየንና ኃጢአታችን በጥምቀት እንደሚነጻ ለማመልከት ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው ከተወለደ በኋላ ፴ (ሠላሳ) ዓመቱ ነው፡፡ የዚህም ምክንያት አባታችን አዳም የሠላሳ ዓመት ፤ እናታችን ሔዋን ደግሞ የዐሥራ አምስት ዓመት ሆነው ሲፈጠሩ አዳም በ፵ (ዐርባ) ቀን፣ ሔዋን በ፹ (ሰማንያ) ቀን ከሥላሴ የተቀበሉትን ልጅነት ጠላታችን ዲያብሎስ ዕፀ በለስን በልተው እንዲሳሳቱ ባደረጋቸው ሰዓት የሥላሴን ልጅነት በማጣታቸው ጌታችን በሠላሳ ዓመቱ ተጠምቆ መልሶላቸዋል፡፡ ዛሬ ወንዶች በዐርባ ቀን፣ ሴቶች በሰማንያ ቀን በዕለተ ዓርብ ከቀኝ ጎኑ በፈሰሰው ማየ ገቦ ተጠምቀን ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ሁለተኛ የምንወለድበት ምክንያትም አዳም በዐርባ ቀኑ፣ ሔዋን ደግሞ በሰማንያ ቀኗ ከሥላሴ ያገኙትን ልጅነት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ (ኩፋ. ፬፥፱) የምንጠመቀውም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው፡፡ ‹‹ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ስታጠምቋቸውም በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው›› እንዲል፡፡ (ማቴ. ፳፰፥፲፱)

ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ‹‹ሖረ ኢየሱስ እምገሊላ ኀበ ዮሐንስ ከመ ያጥምቆ በፈለገ ዮርዳኖስ›› በማለት እንደተናገረ በቅዱስ ዮሐንስ እጅ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በመሄድ በመጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እጅ ተጠመቀ፡፡ የተጠመቀበት ሰዓትም ከሌሊቱ ዐሥር ሰዓት ላይ ሲሆን ዕለቱም ዕለተ ሠሉስ ወይም ማክሰኞ ነበር፡፡ በዮርዳኖስ ወንዝ የተጠመቀበት ምክንያት ደግሞ ጠላት ዲያቢሎስ የዕዳ (የበደል) ደብዳቤያችንን በዚያ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ቀብሮት ስለነበር በጥምቀቱ የዕዳ ደብዳቤያችንን ለመደምሰስ ነው፡፡ ጌታችን በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ ከሰማይ አብ በደመና ሆኖ ‹‹የምወደው ልጄ ይህ ነው፡፡ እርሱን ስሙት›› በማለት የባሕርይ አባትነቱን መሰከረ፤ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ አረፈ፡፡ (ማቴ.፫፥፲፫-፲፯)

በዚህም መሠረት በዓለ ጥምቀት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀበት ከ፴ ዓመት ምሕረት ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በየዓመቱ ጥር ፲፩ ቀን ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ሲከበር ይኖራል፡፡

እኛም የበዓሉን መታሰቢያ የምናደርገው እርሱ ጥምቀትን ስለባረከልን ጥምቀት ድኅነታችን መሆኑን አምነን ተጠምቀን እንድን ዘንድ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እኛ ሁላችን በሞቱ እንደተጠመቅን ሁላችሁ ይህን ዕወቁ፤ እኛ ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛ በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን›› በማለት በጥምቀት ክርስቶስን እንደምንመስለው ተናግሯል፡፡ ይህም ማለት ጌታችን እንደተጠመቀ እርሱን ክርስቶስን መስለን ክርስቲያኖች እንድንባል መጠመቅ እንዳለብን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ (ሮሜ ፮፥፫-፬)

ልጆች! እናንተም በጥምቀት በዓል ከቤተ ሰቦቻችሁ ጋር ሆናችሁ በሥርዓቱ መሠረት እንድታከብሩ እየመከርናችሁ የዛሬን ትምህርት በዚሁ እንጨርሳለን፤ በደኅና ሰንብቱ!

*ከበዓለ ጥምቀቱ ረድኤት፣ በረከት ያሳትፈን! አሜን፡፡*

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# በዓል እና ባህል

**ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ**

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በርካታ መንፈሳዊ በዓላት አሉ። እነዚህም በዓላት በየሀገሩ፣ በየወገኑ፣ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሥርዓት መሠረት ይከበራሉ። ለምሳሌም በዓለ ልደት፣ በዓለ ጥምቀት፣ በዓለ ሆሳዕና ወዘተ በተለያየ ቀን፣ በተለያየ ሥርዓት፣ በተለያየም የባህል ዐውድ ውስጥ ይከበራሉ። የግብጹን ከኢትዮጵያ፣ የሶርያውን ከአርመን የሚለየው ብዙ ሥርዓት ሊኖር ይችላል። ይሁን እንጂ የበዓሉን ማእከልና ዓላማ ግን አንድ ነው እርሱም የበዓሉ ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ማመስገን ነው።

አብያተ ክርስቲያናት ክርስቶስን በበዓሉ በመስበክ፣ በማክበር፣ በበዓሉም መባረክን በመፈለግ በኩል አንድ ዓይነት መንፈሳዊ ዓላማ ስላላቸው የአንድ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ መሆናቸውን ይመሰክራሉ።

በዓላት የሚከበሩበት የባህል ዐውድ ግን ከበዓሉ ዓላማ በላይ ከዋለ፣ በበዓሉ ዕለት ከሚነበበው ወንጌል፣ ከሚነገረው ተአምር፣ ከሚሰበከው ስብከት በላይ በዓሉን ለማድመቅ ተብለው የገቡ በየጊዜው የዳበሩና እየተጨመሩ ያሉ አላባዎች ከገነኑ፤ የበዓሉም ዓላማ የበዓሉን የአከባባር መንገድና ጌጣጌጦች ማንገሥ ላይ ካተኮረ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ያለውን የበዓል መንፈስ እጅግ እያራራቀው፣ ሌላው ቀርቶ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንኳን በዓሉ ልዩ ልዩ ባህል ባላቸው ማህበረሰቦች መካከል መራራቅን ሊያስከትል ይችላል።

ለምሳሌ በዓለ ጥምቀት ሲከበር በየባሕረ ጥምቀቱ በየጊዜው የሚጨመሩ ማድመቂያ ነገሮች የበዓሉን አክባሪዎች ትኩረት ወደሚከብረው ሳይሆን ወደ ማክበሪያው መንገድ እየሳበው ይመስላል። በየባሕረ ጥምቀቱ ደምቀው የሚከናወኑ የቁማር ጨዋታዎች፣ በየድንኳኑ ያሉ የንግድ ትርዒቶች፣ በየምእመኑ የሚደረገው የባህል ልብስ ትዕይንት፣ ከአርሞሪካው ጭፈራ እስከ ምንጃሩ ረገጣ የሚከናወነው ትርዒት ሁሉ ለበዓሉ አክባሪ ግርዶሽ ሆኖ ወደ ዋናው ዓላማ እንዳያተኩር እንቅፋት እየሆኑት ነው።

ባህል መጠበቅ ማክበር መልካም ቢሆንም ምእመናን ከቤታቸው ገና ሲወጡ የክርስቶስን ጥምቀትና በጥምቀቱም የደመሰሰልንን ዕዳና የሰጠንን ጸጋ ሳይሆን ከላይ የተጠቀሱትንና ያልተጠቀሱትን ልዩ ልዩ ክዋኔዎች በዓይነ ኅሊናቸው አዝለው ለመውጣት የሚፈተኑበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። ከዝማሬው፣ ከእልልታው ይልቅ በየጥጋጥጉ በሚገኙ ማረፊያ መጠጥ ቤቶች ጎራ ብሎ ቢራና ድራፍት እየጠጡ ስለፖለቲካው፣ ስለኢኮኖሚው፣ ስለኑሮ ውጣ ውረድ ሁሉ ሲያወጉ መቆየት በስፋት እየተለመደ ነው። ይህም እንደ ባህል ሆኖ ከበዓሉ የጎንዮሽ በስፋት በቅሏል። መንፈሳዊ በዓላትን በወጉ አክብሮ በመብላት በመጠጣት የበለጠ በዓሉን መዝከር ያለና የነበረ ነው። ነገር ግን በዓል ማክበር ቁማሩ፣ ቢራና ድራፍቱ፣ የኮረዶች መሽኮርመም የጎረምሶች ማሽኮርመም ወዘተ እየሆነ ከቀጠለ ሃይማኖታዊው በዓል ሥጋዊ መልኩ ጎልቶ መንፈሳዊ ዓለሙ ደብዝዞ ወደ መጥፋት ይሸጋገራል።

በዓሉ የንግድ ትርዒት መጥሪያ እየሆነ መምጣቱ በበዓሉ አደባባይና ዐውድ ከእምነቱ ውጪ የሆኑ ወገኖች ጭምር የሚሳተፉበት ክፍተኛ የንግድ ክንውን ይታያል። አሁን አሁን በዓሉ መንፈሳዊውን ነገር በማጉላት ከሌላ እምነት የመጡ ወገኖችን እንኳን ሊሰብክና ሊያስተምር በሚችል መንገድ እየተካሄደ አይደለም። ስለዚህ ብዙዎች ነግደው አትርፈው ለመሄድ በጉጉት የሚጠብቁት በዓል እንጂ በምናንጸባርቀው መንፈሳዊ ትዕይንት ተገርመው ‹‹ምን ማለት ነው?›› ብለው እንዲጠይቁን የሚያደርግ አይደለም።

ካህናቱና መዘምራን የበዓሉን ዓላማ ማእከል አድርገው አገልግሎታቸውን መፈጸማቸው እነሱን ተከትሎ ምእመናን ሁሉ አሜን እንዲሉ በማሰብ ነው። ነገር ግን የካህናቱ ሽብሸባ የመዘምራኑ እልልታ ተቀባይና አጃቢ እያጣ ምእመናን በሌላ የባህል ድንኳኖች ውስጥ ገብተው መለያየቱ ከሰፋ የቤተ ክርስቲያን በዓላት የካህናትና የሰንበት ተማሪዎች ብቻ ሆነው ሊንሳፈፉ ይችላሉ።

ከዚህ በተጨማሪም የባህል ፈጠራ ማስፋፋቱ በየአህጉራቱ ልዩ ልዩ መልክ እየያዘ ስለመጣ የትኩረት ማእከሉ ባህል በሆነ መጠን በመንፈሳዊው በዓል ማእከልነት አንድነታችንን ማጽናት እንቸገራለን። በመላው ምእመናን መካከል አንድ መንፈስ ይዞ ክርስቶስን በማሰብ መመላለስ ይቀራል።

በበዓለ ጥምቀት ብቻ ሳይሆን በሌሎች መንፈሳዊ በዓላት ከቤተ ክርስቲያናዊ ሥርዓቱ ይልቅ በቤት ውስጥ መስተንግዶ፣ በዳቦው በቅርጫው በዶሮ ገበያው ወዘተ ነፍሳት ተይዘው በዓሉ ገብቶ እስኪወጣ የበዓሉን ባለቤት በወጉ ሳያስቡ የሚያልፍባቸው በርካቶች ሆነዋል። ቅዳሴው፣ ማኅሌቱ፣ ጸሎቱ... ወዘተ የጥቂቶች ብቻ እየሆነ እየቀረ ነው።

በዓላችንን የሚመሩት ሚዲያዎች እንጂ ቤተ ክርስቲያን መሆኗ እየቀረ ነው። ሚዲያዎች ደግሞ ባህላዊ ይዞታዎች ላይ፣ ንግድ ትርዒትና ባዛሮች፣ የሙዚቃ ድግሶች ላይ፣ በዓሉን ተከትለው በሚዘጋጁ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚያዘጋጇቸው ልዩ ልዩ ክዋኔዎች ላይ አተኩረው ነው። ስለዚህ በዓላችን በአዲስና በነባር የባህል እሴቶች እየተደፈቀ ነው፤ ከቀደመው በባሰ መልኩ የመንፈሳዊው በዓል ዓላማና ተግባር ተሳታፊዎች ጥቂት ምእመናን እንዲሆኑ እያስገደደ ነው። በዓላችን እየመራ ካልሄደ ባህል የሚመራው ከሆነ ሃይማኖታዊ መልኩ ይጠፋል።

**በዓሉ የንግድ ትርዒት መጥሪያ እየሆነ መምጣቱ በበዓሉ አደባባይና ዐውድ ከእምነቱ ውጪ የሆኑ ወገኖች ጭምር የሚሳተፉበት ክፍተኛ የንግድ ክንውን ይታያል። አሁን አሁን በዓሉ መንፈሳዊውን ነገር በማጉላት ከሌላ እምነት የመጡ ወገኖችን እንኳን ሊሰብክና ሊያስተምር በሚችል መንገድ እየተካሄደ አይደለም።**

በመሆኑም እኛ ክርስቲያኖች ሌሎችም ወገኖች እስከሚታዘቡት ድረስ ሥጋዊ መልኮቻቸው እየጎሉ የመጡትን የበዓላት አከባበራችን ወደ ቀደመ ክብርና ለዛቸው መመለስ የዘመናችን አገልጋይ ካህናት ኃላፊነት ይሆናል። ሊቃውንቱ በበዓላቱ መድረኮች ሁሉ ከዚህ አንጻር ምክርና ተግሳጽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ምእመናንም የሊቃውንቱን ምክር ሰምተው ነገሮቻቸው ሁሉ የበዓሉን መንፈሳዊ ዓላማ የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑ መትጋት ይገባቸዋል።

# ''በደረሰብኝ ተደጋጋሚ ችግር ሰዎችን ጠላሁ''

***ይድረስ ለምሥጢሬን ላካፍላችሁ አዘጋጆች፤ እንደምን ከረማችሁ? ቸርነቱ የማያልቅበት እግዚአብሔር አምላክ የተመሰገነ ይሁንና ይህን ጽሑፍ ወደ እናንተ ለማድረስ አብቅቶኛል። እናም ችግሬን ትጋሩኝ ዘንድ በእግዚአብሔር ስም እጠይቃለሁ።***

በጎልማሳነት ዕድሜ ላይ እገኛለሁ፤ ዛሬ ላይ ሆኜ የትናንት ሕይወቴን ሳስብ እጅግ ይከፋኛል፤ ብዙ ችግርና መከራም ያሳለፍኩ ሰው በመሆኔ ኑሮዬ መራር ነው። በተለይም ከወጣትነት ዕድሜ ጅማሮ እስከ አሁን ድረስ በተደጋጋሚ ግፍና በደል ደርሶብኛል፤ ሰዎች የእኔን ፍላጎት ከመጋፋት ጀምሮ በተለያየ መንገድ ጉዳት አድርሰውብኛል። የቅርብ ሰዎች በመሆናቸውም ጉዳቱን እጥፍ አድርጎታል፤ ከዚያም ባሻገር አካላዊ ጥቃትን ያደረሱብኝ እነዚሁ ሰዎች በሕይወቴ ትልቅ የቁስል ጠባሳ አሳርፈውብታል። ምክንያት ለሌለው ነገር ወንድን ለማጥቃት በሚጠቀሙበት ጉልበትም ደብድበውኛል፤ አንዴ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ ነበር፤ እንደዚህ አድራጊዎቹም አብሬአቸው ያደኩና የኖርኩ መሆኑ ችግሩን የባሰ የከፋ አድርጎብኛል። ይህ ሲደጋገምም የማንነት ጥይቄም አስነስቶብኝ ነበር፤ እነርሱንም ቤተሰቦቼ ብዬ ማሰብ እስኪያቅተኝ ድረስ አስጨነቀኝ፤ ድፍረተ አግኝቼም በጠየኳቸው ጊዜ ተገቢውን ምላሽ ሳይሰጡ አስተባብሎ ማለፍን መረጡ።

ከዚሁ በተጓዳኝ ለአቅመ ሔዋንም በደረስኩ ጊዜ ለሕይወት አጋር ሊሆኑኝ ይችላሉ ብዬ ያሰብኳቸው ወንዶች ለትዳር ሳይሆን ለሥጋዊ ፍላጎት ብቻ የሚፈልጉኝ ሆኑብኝ፤ ይህም ጥላቻዬን አባባሰው። በሥራም ሆነ ማኅበራዊ ሕይወቴ ሰዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በተደጋጋሚ ጉዳት አድርሰውብኛል። ከቤተሰብ ጋርም ያለው ሁኔታ እየባሰ በመምጣቱ ከእነርሱ ጋር መኖር የማልችልበት ደረጃ ላይ ደረስኩኝ። ምንም እንኳን ያጠራቀምኩት ገንዘብ ባይኖረኝም የራሴን ሕይወት ለመመሥረት ከበቤተሰቦቼ ወጥቼ ብቻዬን መኖር ጀመርኩ። በዚህም ተጽዕኖ ሰዎች በሕይወቴ ቦታ እንዲኖራቸው አልፈልግም። አዳዲስ ሰዎችንም የመቅረብ ምንም ዓይነት ፍላጎት የለኝም። በአጋጣሚዎች የማገኛቸውንም ከአንገት በላይ በሆነ ቀረቤታ እቀርባቸዋለሁ። በተለያዩ አጋጣሚዎች የተዋወኳቸውንም ደግሞ ለሴት ጓደኝነትም ሆነ የሕይወት አጋርነት ማሰብ እየተሳነኝ እቸገራለሁ። እውነተኛ የሴት ጓደኛም ሆነ ጥሩ ወንድ የለም እስከማለት ደርሻለሁ። ነገር ግን ይህ አመለካከት በእኔ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አምጥቷል፤ ማኅበራዊ ሕይወትም እንዳይኖረኝም አድርጓል፤ ጥላቻዬም እያደረ ክፋት አሳስቦ ወደ ጥፋት እንዳይመራኝ እባካችሁ እርዱኝ እላለሁ።

ውድ የምሥጢሬን ላካፍላችሁ ጠያቂያችን በቅድሚያ መንፈሳዊ መፍትሔ አገኛለሁ ብለሽ ጥያቄውን ስላቀረብሽ እያመሰገንን ለጥያቄው የሚከተለውን ምላሽ አቅርበናል።

ወድ ጠያቂያችን ከጥያቄሽ ለመረዳት እንደቻልነው በገዛ ቤተ ሰብሽ ውስጥ የተለያዩ የአንቺን ፍላጎት የሚጋፉ ፣ብሎም አካላዊ ጥቃት እንዳደረሱብሽ ገልጸሻል። በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጸው ‹‹ በምድር ላይ የሰው ሕይወት ብርቱ ሰልፍ አይደለምን?›› ኢዮ ፯፥፩ ይላል። እንዲሁም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ›› ዮሐ ፲፮፥፴፩ ብሏል። ስለዚህ የሰው ሕይወት ፈተና እና ውጣ ውረድ እንደማይለየው በመጀመሪያ መረዳት ተገቢ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደገለጸው በምድር ላይ የኢዮብን ያህል ፈተና የተፈራረቀበት ሰው ማግኘት ይከብዳል። ጻድቁ ኢዮብ ዐሥር ልጆቹን በአንድ ቀን ያጣ፤ ሀብቱ ሁሉ በአንድ ቀን የወደመበት፣አካሉ ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ፀጉሩ ድረስ በክፉ ቁስል የተመታ ነበር። በትዳር አጋሩ (በሚስቱ) እና በጓደኞቹ ሳይቀር የተለያየ መከራን በጸጋ የተቀበለ ሰው ነው። ነገር ግን ኢዮብ ይህን ፈተና ሁሉ በትዕግሥት ከተቀበለ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ የጻድቁ ኢዮብ ጽናቱን አይቶ ሀብቱን እጥፍ ድርብ አድርጎ መለሰለት።

ሐዋርያው ያዕቆብ ይህን ሲመሰክር ‹‹ወንድሞች ሆይ የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያትን ተመልከቱ፡፡ እነሆ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን ኢዮብ እንደታገሠ ሰምታችኋል ጌታም እንደፈጸመለት አይታችኋል፡፡ ›› ያዕ ፭፥፲፩ በማለት ጻድቁ ፈተናውን በጽናት ከተወጣ በኋላ የተደረገለትን በረከት ይነግረናል፡፡ ‹‹ እግዚአብሔርም ቀድሞ በነበረው ገንዘቡ ሁሉ ፋንታ ከዚያ በላይ አድርጎ ለኢዮብ ሰጠው›› (ኢዮ ፵፪፥፲) በማለት ያረጋግጥልናል፡፡

ይህ ሁሉ ፈተና የደረሰበት እርሱ ጻድቁ ኢዮብ ማነው? ብለን በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጻድቁ ኢዮብ የተጻፈውን ስናይ ኢዮብ

፩ኛ. ፍጹም ነው

፪ኛ. ቅን ነው

፫ኛ. እግዚአብሔርን የሚፈራ ነው

፬ኛ. ከክፋትም የራቀ መሆኑ የተመሰከረለት ጻድቅ ሰው ነው ኢዮ ፩፥፩-፪፡፡

ውድ ጠያቂያችን በጻድቁ ኢዮብ ሕይወት አንጻር ፈተና ደርሶብኝ ቤተሰቦቼን እስክጠላቸውና እስክጠራጠራቸው ያደረሰኝ ሕይወት ላይ ነኝ ፤ እንዲሁም የአካል ጉዳት ደርሶብኛል የሚለውን ኃሳብ ጻድቁ ከደረሰበት ፈተና አንጻር የእኔ ሕይወት እንዴት ነው ብለሽ መመልከቱ በተወሰነ መልኩ ለጥያቄሽ መልሽ ይሰጥሻል፡፡

ከላይ እንደገለጽነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ›› በማለት ማስተማሩ የዚህን ዓለም መከራና ሥቃይ አስቀድመን እንድናውቀውና አዲስ ነገርም እንዳይሆንብን ጭምር ነው፡፡ ጌታችን ‹‹ እኔን መከተል ቢወድ ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ›› ማቴ ፲፮፥፳፬ ብሎ ማስተማሩን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይገባል፡፡ ለመሆኑ ራስን መካድ ማለት ምን ማለት ነው? እኔ ሰው አይደለሁም ማለት ነውን? በእርግጥ እንዲህ ማለት አይደለም፡፡ ውድ ጠያቂያችን ራስን መካድ ማለት እውቀት፣ ሀብት ፣ ሥልጣን ፣ዘመድ ቢኖር በእርሱ አይመካ ማለቱ ነው፡፡ ‹‹ የሚመካ ቢኖር በእግዚአብሔር ይመካ እንዲል ›› ፩ኛ ቆሮ ፩፥፴፩ ፡፡

ከላይ እንዳየነው መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ ማለት ‹‹በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ›› ተብሏልና የደረሰብንን ግፍና መከራ በአኮቴት (በምስጋና) ተቀብሎ እንደ ኢዮብ በፈተና መጽናት ማለት ነው፡፡ ‹‹ወንድሞች ሆይ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደሙሉ ደስታ ቁጠሩት›› (ያዕ ፩፥፪-፫) እንዳለ ቅዱስ ያዕቆብ በደረሰብሽ ፈተና ሳትማረሪና ተስፋ ሳትቆርጪ እንደ ሙሉ ደስታ ልትቆጥሪው ይገባል፡፡

ይህ ፈተና በቅድሚያ የደረሰብሽ ከቤተሰቦችሽ በመሆኑ የእምነትሽን ጽናት ለማየት የቀረበልሽ ፈተና መሆኑን መገንዘብ ይገባሻል፡፡ በመጽሐፈ ኢዮብ ‹‹ ዓለም ሁሉ ዞርኳት›. ያለው ጥንተ ጠላታችን ቤተሰቦችሽ በአንቺ ላይ እንዲነሳሱ እና የአካል ጉዳትም ጭምር እንዲያደርሱብሽ ያደረገው ፈታኝ (ዲያቢሎስ)መሆኑን ልታወቂበት ይገባል፡፡ ‹‹ ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ››(ያዕ ፭፥፲፫) እንዳለው በቤተሰቦችሽ ላይም ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ ቶሎ ተስፋ ወደ መቁረጥ ሳትሄጂ ‹‹ የደረሰብኝ መከራ ለበጎ ነው›› ብለሽ ኀሊናሽን አሳምነሽ ከሁሉ በፊት ጸሎትን የሕይወትሽ አንድ ገጽታ አድርገሽ ልትኀዢ ይገባል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመልዕክቱ ‹‹በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ›› (ፊል ፬፥፯) እንዳለው  በነገር ሁሉ ሲል በጥቂትም በብዙም ፣ በውስጥም በውጪም ፤ በሚታየውም ሆነ በማይታየው ሁሉ ነገር ሲያጋጥማችሁ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ እንድናስታውቅ ያዛልና ይህን የሕይወት መመሪያ ልታደርጊው ይገባል፡፡

ለደረሰብሽ ነገር ሁሉ በቅድሚያ በጸሎት እግዚአብሔርን መጠየቅ ይገባሻል፡፡ ስትጸልይ ደግሞ ሐዋርያው በምልጃ እንዳለ ስለናትህ ቅድስት ድንግል ማርያም ብሎም ስለቅዱሳንህ ሁሉ ብለህ የዚህን ፈተና መውጫ መንገዱን አመልክተኝ ብለሽ መለመን ይገባሻል፡፡ ስለደረሰብሽ ነገር ሁሉ ደግሞ ሳትማረሪ እግዚአብሔርን አመስግኝ፡፡ ‘’እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት

ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን” (ሮሜ ፰፥፳፰) ተብሎ ተጽፏል።

ከዚህም በተጓዳኝ ከቤተሰቤ ተለይቼ ብቻዬን እየኖርኩ እገኛለሁ ብለሻል። ለመሆኑ አንቺ የዘረዘርሻቸውን ፈተና ያደርሱብሽ ቤተሰቦችሽ ወደው ይመስልሻል? ስለሆነው ነገር ሁሉም ለቤተሰቦችሽም ጸልይላቸው። እንኳን ቤተሰቦችሽ ይቅርና ሌላም አካል ይህንን ፈተና ቢያደርስብሽ ልትጸልይለት ይገባል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁንም መርቁ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሰድዷችሁም ጸልዩ” (ማቴ ፭፥፵፬ ) ብሏልና።

አበው “እባብ ያየ በልጥ ይደነግጣል” እንዲሁ እንጂ በቤተሰቦችሽ ከደረሰብሽ ፈተና የተነሳ ሰውን ሁሉ ወደ መጠራጠር ተጉዘሻል። እኔ ለትዳር ያሰብኳቸውም እንኳን ቢሆኑ እነርሱ ግን ለሥጋዊ ፍላጎት ብቻ የሚፈልጉኝ ሆነብኝ ምን ይሻለኛል? ላልሽው በመጀመሪያ ከትዳሩ በፊት አንቺ ሕይወትሽ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የታነጸ ይሆን ዘንድ ቅድሚያ የነፍስ አባት ይዘሽ ዘወትርም በፀሎት እየተጋሽ ተጓዥ። ጌታችን ለምጻሙን ሰው ካዳነው በኋላ “ሂድ ራስህን ለካህን አሳይ” (ማቴ ፰፥፬) በማለት እንዳዘዘው አበነፍስ ይዘሽ የተሰጠሽን ቀኖና በተግባር ፈጽሚ። ከዚህም በተጓዳኝ ወደ ቅዱሳት መካናት እየተጓዝሽ አበው በጸሎታቸው እንዲያስቡሽ አስደርጊ “የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች” (ያዕ ፭፥፲፮) ይላልና።

እውነተኛ የሴት ጓደኛም ሆነ ጥሩ ወንድ የለም እስከ ማለት ደርሻለሁኝ ያልሽውም ስሕተት መሆኑን በቅድሚያ ለኅሊናሽ ንገሪው ምክንያቱም ሁሉም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ስሑታን ናቸው ብሎ ለመቀበል ይከብዳልና። በመጽሐፍ “ከቸር ሰው ጋር ቸር ሁነህ፣ ከቅን ሰው ጋር ቅን ሁነህ፣ ከንጹሕ ጋር ንጹሕ ሁነህ ትገኛለህ፣ ከጠማማ ሰው ጋር ጠማማ ሁነህ ትገኛለህ” (መዝ ፲፯፥፳፭-፳፮) ተብሏልና።

ከወንድም ሆነ ከሴት ጓደኞችሽ ቸር፣ ቅን፣ ንጹሕ የሆኑ እንዳሉ ሁሉ ጠማማ የሆኑም ሊኖሩ እንደሚችሉ እንጂ ሁሉንም ሰው አንድ ዓይነት ጠባይ አላቸው ብለሽ አትራቂያቸው። ከመንፈሳውያን ጓደኞችሽ የምታገኚው ጠቃሚ ምክር መኖሩንም አትዘንጊ።

አበው‹‹ ሰይጣን ተስፋ የለውም፤ ግን ተስፋ አይቆርጥም›› የሚል ብሂል አላቸው። ክርስቲያን ደግሞ ተስፋ እያለው ተስፋን መቁረጥ አይገባውም ይልቁንም ‹‹አሁንስ ተስፋዬ ማነው? እግዚአብሔር አይደለምን? ትዕግሥትም ከአንተ ዘንድ ነው››(መዝ ፴፱፥፯) በማለት እንደ ቅዱስ ዳዊት ተስፋሽን በእግዚአብሔር ላይ አድርገሽ በትዕግሥት ነገሮችን ሁሉ እንደአመጣጣቸው ትቀበዪ ዘንድ ይገባል።

ውድ ጠያቂያችን በዚህ ሰዓት ከሁሉ ማስቀደም ያለብሽ ጉዳይ ከቤተሰብሽ፣ የትዳር አጋር ከመፈለግሽ፣ ከጓደኛም በፊት ሕይወትሽ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያማረ ይሆን ዘንድ ዘወትር ስለነፍስሽ አስቢ፣ ንሰሓ ግቢ፣ በጸሎት በርቺ፣ በጸሎት እንዲያስቡሽ ወደ ቅዱሳን መካናት ስመ ክርስትናሽን ከመብአ ጋር ላኪ። በተጨማሪም ስለደረሰብሽ ነገር ሁሉ ሳታማርሪ እግዚአብሔርን አመስግኚው። እግዚአብሔር አምላክ በነቢዩ ኤርምያስ አድሮ ‹‹ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም›› (ኤር ፳፱፥፲፩) ብሏልና የሰላም አምላክ ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንቺ የሚያስፈልግሽን እንደሚሰጥሽ አምነሽ በጸሎት ተማፀኚ። ከላይ በመግቢያሽ የዘረዘርሻቸውን ፈተናዎች እንድትቋቋሚው ኃይል የሰጠሽ አማላክ ካንቺ ጋር መሆኑን እመኚ።

ጌታችን በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ሆኖ ለሰቃዮቹ እንዳዘነላቸውና እንደራራላቸው በአንቺ ላይ ክፉ ነገር ላደረሱብሽ ሁሉ ‹‹አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው›› እያልሽ ጸልይላቸው። ሊቀ ዲያቆናት ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስም በድንጋይ እየወገሩት እርሱ ግን ወደ አምላኩ እንደጸለየላቸው አንቺም አውቀሽ ጸልይላቸው። ይህ ሁሉ አልፎ፣ ሐሳብ ተሳክቶ ለምስጋና የምትቆሚበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን እመኚ። ስለሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት የቅዱሳን ሁሉ ተራዳኢነት ካንቺ ጋር ይሁን።